Washington
Apple Health

Washington Apple Health (Medicaid) የጀማሪዎች መመሪያ

የዚህ መመሪያ ክፍል 1 ለመጀመር ያስችሎታል። ይህ ክፍል ለተወሰኑ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።
ክፍል 2 ለመጀመሪያ ጊዜ የህክምና አገልግሎት ሰጪ ጋር ስሄዱ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ምክር ይሰጣል።

ክፍል 1: እርስዎ በApple Health ከተመዘገቡ በኋላ

እኛ ወደ Washington Apple Health እንኳን በደህና መጡ የሚል በራሪ ወረቀት ስለሸፋንዎ ከሚያወሱ ጠቃሚ መረጃዎች ጋር በፖስታ እንልክልዎታልን። እርስዎ ይህንን በራሪ ወረቀት በድህረ ገጻችን ላይ ያገኛሉ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf.**

የእርስዎ የጤና አቅድ ተቋምም ለእርስዎ መረጃዎች ይልካል።

ይህ የእርስዎ የአገልግሎት ካርድ ነው።

እርስዎ በWashington Apple Health ላይ ከተመዘገቡ ከሁለት ሳምንት በኋላ ምስሉ እዚህ ከሚታየው ጋር ተመሳሰይ የሆነ የአገልግሎት ካር (ProviderOne ተብሎም ይጠራል) ይቀበላሉ። ይህንን ካርድ ይያዙ። የእርስዎ የአገልግሎት ካርድ እርስዎ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚፈልጉትን የእርስዎን የደንበኛ ቁጥር ያሳያል። እርስዎ አዲሱን የአገልግሎት ካርድ እንዲሰራ ማድረግ አይጠበቅብዎትም። ካርዱ ለእርስዎ ከመላኩ በፊት እንዲሰራ ተደርጓል።

የApple Health አገልግሎት ለማግኘት ብቁ የሆነ እያንዳንዱ የቤተሰብዎ አባል የራሱ የአገልግሎት ካርድ ይወስዳል። እያንዳንዱ ግለሰብ በህይወት ዘመኑ አብሮት የሚቆይ የተለየ የደንበኛ ቁጥር ይኖረዋል።

እርስዎ ከዚህ ቀደም የApple Health ሽፋን ካለዎት (ወይም Apple Health ተብሎ ከመሰየሙ በፊት የMedicaid ሽፋን ካለዎት) እኛ ለእርስዎ አዲስ ካርድ አንልክልዎትም። ምንም እንኳን እርስዎ በተከታታይ ሽፋን ባይኖርዎትም የእርስዎ አሮጌው ካርድ አሁንም ድረስ ተቀባይነት አለው። የእርስዎ ደንበኛ ቁጥር ተመሳሳይ ሆኖ ይቀጥላል።

በአገልግሎት ካርድዎ ላይ "ProviderOne" የሚል ፅሁፍ ያገኛሉ።

ProviderOne የጤና እቅድ የሚመራ የኮምፒተር ሲስተም ነው። ሲስተሙ ደብዳቤዎችና መጽሀፍት ይልክልዎታል። በካርዱ ላይ የሰፈረው ቁጥር የProviderOne ደንበኛ ቁጥር ነው።

Washington State
Health Care Authority

የጤና ክብካቤ ባለሥልጣን Washington Apple Health (Medicaid) ያስተዳድራል።

HCA 19-024 AM (7/16) Amharic

ሚስጢርዎን መጠበቅ

እርስዎ አገልግሎት ካርድ ከስምዎመ የProviderOne የደንበኛ ቁጥር እና የተሰጠበት ቀን በስተቀር ማንኛውንም የግል መረጃዎች አያካትትም። ካርዱ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ ሚስጢርዎ ይጠበቃል።

Apple Healthም ሆነ የእርስዎ የጤና እቅድ የአገልግሎት ካርድ ለመቀበል ወይም ለመተካት የግል መረጃዎችዎን ለመጠየቅ በቀጥታ አያነጋግርዎትም። እንደማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ያሉ የግል መረጃዎችን ለሚደውልልዎት ወይም በኢሜይል ለሚልክልዎት ማንኛውም ግለሰብ አይሰጥም። አንድ ግለሰብ የእርስዎን ማህበራዊ ዋስትና ቁጥር ከጠየቀዎት እባክዎን ስማቸውንና የግንኙነት መረጃቸውን ጨቀው ወደ ደንበኛ አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 ደውለው ሪፖርት ያድርጉ።

እርስዎ ካርድ ካልተቀበሉ

እርስዎ የApple Health ማመልከቻዎን ከሞሉ በኋላ በሁለት ሳምንታት መጨረሻ ላይ የአገልግሎት ካርድዎን ካለወሰዱ በነጻ ምትክ ካርድ ለማግኘት የProviderOne የደንበኛ መግቢያ በድህረ ገጽ **https://www.waproviderone.org/client** ይጎብኙ

በጤና እቅድዎ ሰጪ ተቋም ዘንድ መመዝገብ

እርስዎ በApple Health በቀጥታ የኢንተርኔት መረብ በድህረ ገጽ **www.wahealthplanfinder.org** በኩል ካመለከጹ እርስዎ ምናልባት በአከባቢው ከሚገኙ የጤና እቅዶች መካከል በአንዱ ተመዝግበዋል። እርስዎ በወቅቱ በጤና እቅድ ካልተመዘገቡ እኛ አንዱን እንመርጥልዎታለን።

ሌላ እቅድ በአከባቢዎ ካለ እርስዎ **www.wahealthplanfinder.org** በመጎብኘት በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። በእርስዎ የጤና እቅድ ላይ የሚደረግ ለውጥ ከቀጣይ ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል። (እቅድዎን ለመለውጥ ያሉትን ሉሎች መንገዶች ለማወቅ በገጽ 4 ላይ ያለውን “Can I change my health plan?” ይመልከቱ።)

ሽፋንዎን ማደስ

የApple Health ምዝገባዎ አብዛኛውን ጊዜ ለአንድ አመት ይቆያል። እርስዎ የApple Health ሽፋንዎን እንዲያዲሱ ለማስታወስ ደብዳቤ እንልክልዎታለን፤ በመሆኑም እርስዎ የደብዳቤ መቀበያ አድራሻዎን ወቅታዊ መረጃዎች ማሳወቅ ጠቃሚ ነው። ደብዳቡው ካርድዎ የታደሰልዎት መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በደብዳቤው ውስጥ ያለ መረጃ ትክክለኛ ካልሆነ በስተቀር እርስዎ ምንም አያደርጉም።
እርስዎ የApple Health አገልግሎትዎን ማደስ ከፈለጉ በደህረ ገጽ **www.wahealthplanfinder.org**, በፖስታ ወይም በስልክ ማደስ ይችላሉ። ደብዳቤው ስለሁሉም አማራጮችዎ በዝርዝር ይነግርዎታል።

አነዚህ አምስቱ የጤና እቅዶችና የግንኙነት መረጃዎቻቸው ናቸው። ሁሉም እቅዶች በግዛቱ ሁሉም ቦታዎች አይገኙም።

ቁጥጥር የሚደረግበት ህክምና የሚሰጥበት የጤና እቅድ	ዋና ስልክ	የነርስ እርዳታ መስመር
Amerigroup Washington Inc. (AMG) **www.myamerigroup.com/wa/pages/welcome.aspx**	1-800-600-4411	1-800-600-4411
Community Health Plan Of Washington (CHPW) **www.chpw.org**	1-800-440-1561	1-866-418-1002
Coordinated Care Corporation (CCC) **www.coordinatedcarehealth.com**	1-877-644-4613	1-877-644-4613
Molina Healthcare of Washington (MHC) **www.molinahealthcare.com/members/wa/en-us/Pages/home.aspx**	1-800-869-7165	1-888-275-8750 በስፓኒሽ ቋንቋ 1-866-648-3537
UnitedHealthcare Community Plan (UHC) **www.uhccommunityplan.com**	1-877-542-8997	1-877-543-3409





የጤና እቅድዎ ካርድ

የእርስዎ የጤና እቅድ ለእርስዎ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። ይህንን ካርድ ይያዙ። ወደ ሀኪም፣ መድሀኒት መደብር ወይም ወደሌላ የጤና እርዳታ ሰጪ ዘንድ ሲሄዱ ሁለቱንም ማለትም የአገልግሎት ካርዶትንና የጤና እቅዶትን ካርድ ይያዙ። ፎቶ ያለበት መታወቂያም ሊያስፈልግዎ ይችላል።

ሊኖርዎት የሚችሉ ጥያቄዎች

እኔ ካርዴን ከሌለኝ የደንበኛ ቁጥሬን እንዴት አገኛለሁ?

ካርድዎ ከመደረሱ በፊት ዶክተር ጋር መሄድ ወይም የሚታዘዝ መድሃኒቶች መሙላት ከፈለጉ እርስዎ አግልግሎቶች የሚያገኙበት ሁለት መንገዶች አለዎት፡፡

- የደንበኛ ቁጥርዎን ለማግኘት የProviderOne የደንበኛ መግቢያ **https://www.waproviderone.org/client** ላይ ገብተው ይጎብኙ፡፡ ያንን ቁጥር ለጤና እርዳታ ሰጪ ወይም ፋርማሲስት ይስጡ፡፡
- ስምዎን፣ የትውልድ ቀንዎን እና ማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ለጤና እርዳታ ሰጪ ወይም ፋርማሲስት ይንገሩ፡፡ እነርሱ የእርስዎን የደንበኛ ቁጥር በቀጥታ የኢንተርኔት መረብ በማፈላለግ ያገኛሉ፡፡

እኔ የአገልግሎት ካርዴን ከጣልኩ ምን ይፈጠራል?

ምትክ ካርድ የምጠየቁበት ብዙ መንገዶች አሉ፡

- የProviderOne የደንበኛ መግቢያ በድህረ ገጽ **https://www.waproviderone.org/client** ይጠቀሙ፡፡
- ለደንበኛ አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 ይደውሉ፡፡
- በቀጥታ የኢንተርኔት መረብ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/client_webform** ለውጥ ይጠይቁ ። “Services Card” የሚለውን ርዕስ ይምረጡ፡፡

አዲሱን ካርድ ለማግኘት ምንም ክፍያ አይጠየቁም፡፡ አዲሱን ካርድ በፖስታ ውስጥ ለማግኘት ከሰባት እስከ 10 ቀናት ይወስዳል፡፡ የእርስዎ አሮጌው ካርድ እርስዎ አዲሱን በሚጠይቁበት ጊዜ መስራቱን ያቆማል፡፡

እኔ የጤና እቅድ ካርዴን ከጣልኩ ምን ይፈጠራል?

ለጤና እቅድዎ በመደወል አዲስ ካርድ እንዲሰጥዎት ይደውሉ፡፡ (የጤና እቅዶች የግንኙነት መረጃዎቸች በገጽ 2 ላይ ይመልከቱ፡፡)

እኔ በApple Health ሽፋን ወይም በጤና እቅድ ውስጥ መመዝገቤን እንዴት ማጣራት ወይም ማየት እችላለሁ?

ሽፋንዎ መጀመሩን ለማየት የፕሮቫደርዋን ደንበኛ መግቢያ በድህረ ገጽ **https://www.waproviderone.org/client** ላይ ገብተው በመጎብኘት ወይም በደንበኛ አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 በመደውል ማጣራት ይችላሉ፡፡ እርስዎ የአገልግሎት ካርድ ቁጥርዎን ወይም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ማወቅ ያስፈልግዎታል፡፡

1. ከዋናው ዝርዝር የራስዎን ቋንቋ በመምረጥ የስልክ አማራጮችን ይከተሉ፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ “የደንበኛ አገልግሎት” ነው፡፡
2. የቀጣይ ጥያቄ መልስ “የሚፈቀድ መሆኑን ያጣሩ” የሚል ነው፡፡
3. ቀጥለው ሲጠየቁ “ቀጥል” ይበሉ፡፡
4. በቀጣዩ ጥያቄ ላይ “የማህበራዊና ጤና አገልግሎት መምሪያ ካርድ” (ይህ ማለት የእርስዎ የአገልግሎት ካርድ) ወይም “የማህበራዊ ዋስትና ካርድ” ብለው በሚያውቁት ቁጥር መሰረት ይመልሱ፡፡ እርስዎ ቁጥሩን መናገር ወይም በቁጥሩ ላይ መደወል ይችላሉ፡፡
5. ጥያቄው የእርስዎን ዚፕ ኮድ ይጠይቃል፡፡
6. ቀጥሎ፣ ጥያቄው ስለራስዎም ሆነ ሌላ የቤተሰብ አባል መረጃዎች ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቃል፡፡
7. በመጨረሻም ሲጠየቁ ለዛሬ ወይም ለሌላ ቀን መመዝገብ የሚፈልጉ መሆንዎን ይናገሩ፡፡ አውቶማቲክ አገልግሎቱ የእርስዎን የምዝገባ ሁኔታ (መመዝገብዎንና አለመዝገብዎን) እና በዚያን ቀን እርስዎ የተመዘገቡበትን የጤና እቅድ ይነግርዎታል፡፡

እኔ በጤና እቅድ መመዝገብ አለብኝ?

አዎ፣ ከጥቂት ማግለያዎች ጋር ለተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች ወደ *Washington Apple Health* እንኳንደህና መጡ የሚለውን መጽሐፍ በ**www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf** ላይ ይመልከቱ፡፡

እኔ የፈለጉትን የህክምና እርዳታ ሰጪ ዘንድ መሄድ እችላለሁ?

አይ፣ የጤና እቅዱ በጤና እቅዱ ኔትዎርክ ውስጥም ሆነ ውጭ ያለ ስፔሻሊስት ጋር እንዲሄዱ የጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጠዎት በስተቀር በእርስዎ የጤና እቅድ ኔትዎርክ ውስጥ ያሉ የህክምና እርዳታ ሰጪዎች ጋር መሄድ አለብዎት፡፡

እርስዎ ልዩ ዶክተር ወይም የጤና ክብካቤ ሰጪ መጠቀም ከፈለጉ ዶክተሩ ወይም እርዳታ ሰጪው በየትኛው የጤና እቅድ ውስጥ እንደሚገኝ ይጠይቁ፡፡ ያ ዶክተር ወይም የጤና እርዳታ ሰጪው በአርስዎ አከባቢ በሚገኝ የጤና እቅድ ውስጥ ያለ ከሆነ እርስዎ የጤና እቅዶችን መለወጥ ይችላሉ፡፡ የተወሰኑት አገልግሎቶች በእርስዎ የጤና እቅድ አልተሸፈኑም፤ ነገርግን በApple Health የአገለግሎት ክፍያ ስር ተሸፍነዋል፡፡ በመሆኑም እርስዎ የApple Health የአገልግሎት ክፍያ የሚቀበል የህክምና እርዳታ ሰጪ ጋር መሄድ ይጠበቅብዎታል፡፡ (“What is fee-for-service?” የሚለውን ገጽ 5 ላይ ይመለከቱ፡፡)

የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ ምንድነው?

የእርስዎ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ ለአብዛኛው ወይም ሁሉም የጤና ክብካቤዎ የሚጎበኙት ዶክተር፣ ነርስ ሐኪም፣ ሌላ የጤና ክብካቤ ባለሙያ ወይም ክሊኒክ ነው፡፡ የእርስዎ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ በእርስዎ የጤና እቅድ ኔትዎርክ ውስጥ መሆን አለበት፡፡

እኔ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ እንዴት አፈላልጋለሁ?

የእርስዎ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ በእርስዎ የጤና እቅድ ኔትዎርክ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ አሁን ካለው የጤና እቅድ ኔትዎርክዎ ውስጥ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ ይምረጡ ወይም እቅዱ እርስዎ አንድ እርዳታ ሰጪ እንዲመርጡ ያግዝዎታል፡፡ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ ለመምረጥ የእርስዎን የጤና እቅድ ድህረ ገጽ ይጎብኙ፡፡ በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ስር ስለጤና እርዳታ ሰጪ አመራረጥ ተጨማሪ መረጃዎች አሉ፡፡

ቀጠሮ እንዴት እይዛለሁ?

የእርስዎ የጤና ክብካቤ እቅድ ቀጠሮ እንዴት እንደሚይዙ የሚመለከቱ መረጃዎችን ይልክልዎታል፡፡ ወይም ለጤና እቅድዎ በመደወል እነርሱ እንዲጀምሩ ሊያደርግዎት ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያ ቀጠሮዎን መያዝ የሚመለከቱ መረጃዎች በዚህ መመሪያ ክፍል 2 ላይ ይመልከቱ፡፡

በቤተሰቤ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ ተመሳሳይ የጤና እቅድ አለው?

አዎ በአጠቃላይ የቤተሰብዎ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ አሜሪካ ኢንዲያን ወይም የአላስካ ተወላጅ ካልሆነ በስተቀር ተመሳሳይ የጤና እቅድ አለው፡፡ ወደ *Washington Apple Health* እንኳንደህና መጡ የሚለው መጽሐፍ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf** ተጨማሪ መረጃዎች አሉት፡፡

በእቅዶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ሁሉም እቅዶች ተመሳሳይ መሰረታዊ አገልገሎቶች ይሸፍናሉ፤ ግን በአገልግሎት አሰጣጥ የተወሰኑ ልዩነቶች አላቸው፡፡ ወደ *Washington Apple Health* እንኳን ደህና መጡ የሚለው መጽሐፍ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf** መሰረታዊ አገልግሎቶችን ይዘረዝራል፡፡

እያንዳንዱ የጤና እቅድ የራሱ የእርዳታ ሰጪዎች መረብ አለው፡፡ እርስዎ የመረጡት የጤና እርዳታ ሰጪዎች በጥላኔ ኔትዎርክ ውስጥ መኖራቸውን ከጤና እቅዱ እባክዎን ያጣሩ፡፡

የጤና እቅዴን መለወጥ እችላለሁ?

አዎ፣ በማንኛውም ጊዜ ለውጡ ከቀጣይ ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የእቅድ ሰጪዎትን ለመቀየር ብዙ አማራጮች ይኖሮታል፡

- እቅድ ሰጪውን በዋሽንግተን የጤና እቅድ አፈላላጊ ድህረ ገጽ ላይ ገብተው ይለውጡ **www.wahealthplanfinder.org**
- የProviderOne የደንበኛ መግቢያ ድህረ ገጽ ይጎብኙ **https://www.waproviderone.org/client**
- ለውጥ በዚህ የቀጥታ የኢንተርኔት መረብ ይጠይቁ **https://fortress.wa.gov/hca/p1contactus/client_webform/** ። “ምዝገባ/የጤና እቅዶች ለውጥ” የሚለውን ርዕስ ይምረጡ፡፡
- ከሚከተለው የድህረ ገጽ አድራሻ የምዝገባ ቅጽ ያትሙ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/13-862.pdf** . በመመሪያዎቹ መሠረት ቅጹን በመሙላት በደብዳቤ መላክ ወይም በፋክስ ቁጥር 1-866-668-1214 ይላኩ.
- ለደንበኛ አገልግሎት ማዕከላችን በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 ይደውሉ፡፡

የትኛውን ፋርማሲ ወይም የመድሃኒት መደብር እጠቀማለሁ?

የእርስዎ የጤና እቅድ የትኞችሁን ፋርማሲዎች እና የመድሃኒት መደብሮች መጠቀም እንዳለብዎት የሚገልጹ መረጃዎችን ይሰጥዎታል፡፡

ከመደበኛ የስራ ሰዓት በኋላ ህክምና የሚፈልግ ከሆነስ?

የእርስዎ የጤና እቅድ ነርስን በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀናት ማነጋገር የሚችሉበት የክፍያ ነጻ ስልክ ቁጥር ይሰጥዎታል፡፡ ስልክ ቁጥሩ የጤና እቅድዎ በላከልዎት መረጃዎች ውስጥ የተካተተ ሲሆን በገጽ 2 ላይ ተዘርዝሯል፡፡

እኔ ድንገተኛ የጤና ችግር ካለብኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

እርስዎ ድንገተኛ ነው ብለው የሚያምኑ ድንገተኛ ወይም ከባድ የጤና ችግር ካለብዎት ለ911 ይደውሉ ወይም ቅርብ ወዳለው የድንገተኛ ህክምና ክፍል ይሂዱ፡፡ ከዚያ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ለጤና እቅድዎ በመደወል ድንገተኛ የጤና ችግር ያጋጠመዎት መሆኑን እና ህክምና ከየት እንዳገኙ ያሳውቁ፡፡

እርስዎ አስቸኳይ ህክምና ከፈለጉ ነገር ግን ለህይወትዎ የማሰጋ ከሆነ ለመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪዎ፣ ለጤና እቅድዎ ወይም የ24 ሠዓት የነርስ እርዳታ መስመር ይደውሉ፡ ስልክ ቁጥሮች ለማግኘት ገጽ 2 ይመልከቱ፡፡

(ካለፈው የቀጠለ)

እኔ የጤና እርዳታ ሰጪ ጋር ሄዶ ለመታከም ወይም የመድሃኒት ማዘዣዎች ለመሙላት መክፈል አለብኝ?

በጤና እቅድዎ የተቀመጡትን ደንቦች እስከተከተሉ ድረስ - አይ

እርስዎ ክፍያ የሚከፍሉት፡

- የካይሮፕራክቲክ ህክምና ወይም የኮስሞቲክ ቀዶ ህክምና የመሳሰሉ ያልተሸፈ አገልግሎት ካገኙ፡፡
- በህክምና አስፈላጊ ያልሆነ አገልግሎት ካገኙ፡፡
- የጤና እቅድዎን ስም የማያውቁ ከሆነ እና እርስዎ የሄዱበት የህክምና እርዳታ ሰጪ የክፍያ ጥያቄውን ለማን እንደሚያቀርብ የማያውቅ ከሆነ፡ ፡ ይህ የአገልግሎት ካርድዎን እና የጤና እቅድዎን ካርድ አገልግሎት ማግኘት በፈለጉበት ጊዜ መያዝ የሚገባዎት ምክንያት ነው፡፡ (ሰለካርዶቹ የሚመለከቱ መረጃዎች በገጽ 1-3 ይመልከቱ፡፡)
- ችግሩ ድንገተኛ ካልሆነ ወይም በጤና እቅድዎ አስቀድሞ ካልጸደቀ ወይም ረፈር ካልተደረገ በስተቀርከጤና እቅድ ኔትዎርክዎ ወጭ ከሆነ አገልግሎት ሰጪ ህክምና ካገኙ።
- ከስፔሻሊስት ህክምና ለማግኘት የእርስዎን የጤና እቅድ ደንቦች ያልተከተሉ ከሆነ።

የአገልግሎት ክፍያ ምንድነው?

Apple Health ዶክተሮችና የአግልሎት ሰጪዎች በቀጥታ እነርሱ ለሰጡት እያንዳንዱ አገልግሎት ክፍያ ስከፍለቸው ይህንን ሂደት የምንጠራበት ቃል ነው፡፡ አብዘኛዎቹ የApple Health ደንበኞች ለመደበኛ የጤና ክብካቤያቸው የአግልግሎት ክፍያ አያገኙም፡፡ አብዘኛዎቹ አብላጫውን አገልግሎቶች በጤና እቅዶቻቸው በኩል "ቁጥጥር የሚደረግበት ህክምና" ያገኛሉ፡፡ (የሚቀጠለው ጥያቄ "ቁጥጥር የሚደረግበት ህክምና ምንድነው?" የሚለውን ይመልከቱ፡፡)

ለእርስዎ የሚሰጡ የተወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞች "የአገልግሎት ክፍያ ጥቅማ ጥቅሞች" ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በግዛት መንግስት የሚሸፈኑ ሲሆን በእርስዎ የጤና እቅድ ሳይሆን በሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ይሰጣሉ፡፡ የገልግሎት ክፍያ እያስከፈል አገልግሎት የሚሰጥ አግልግሎት ሰጪ ለማፈላለግ የProviderOne የአገልግሎት ሰጪ መፈለጊያ መሳሪያ በድህረ ገጽ **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider** ይመልከቱ።

የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልባቸው ጥቅማ ጥቅሞች የጥርስ ህክምና፣ የአልኮል መጠጥ እና የእፅ መጠቀም በሽታ አገልግሎቶች እና ተኝቶ ታካሚ የአእምሮ ህክምና ያካትታል፡፡ የእርስዎ የመጀመሪያ የጤና እርዳታ ሰጪ , ወይም የጤና እቅድ እነዚህን ጥቅማጥቅሞች እንዲያፈላልጉ የሚያግዙዎት ሲሆን የእርስዎን ህክምና ያስተባብራሉ፡፡

የአገልግሎት ክፍያ ጥቅማጥቀሞች ዝርዝር ለማግኘት እባክዎን ወደ *Washington Apple Health* እንኳን ደህና መጡ የሚለው መጽሐፍ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf** ይመልከቱ፡፡

ቁጥጥር የሚደረግበት ሕክምና ምንድነው?

አብዘኛዎቹ የApple Health ደንበኞች "ቁጥጥር የሚደረግባቸው የህክምና አገልግሎት" ያላቸው ሲሆን ይህ ማለት Apple Health ለእርስዎ ህክምና ወርሃዊ ክፍያ ለጤና እቅድ ተቋም ይከፍላል ማለት ነው፡፡ የጤና እቅድ ተቋም ከዚያ እርስዎን ላከመው የጤና እርዳታ ሰጪ ይከፍለል፡፡ አብዘኛዎቹ የApple Health ደንበኞች ለአብዘኛዎቹ አገልግሎታቸው ቁጥጥር የሚደረግባቸው ወይም የታዘዘላቸውን ህክማና ይወስዳሉ፤ ግን የተወሰኑት አገልግሎቶች "በአግልግሎት ክፍያ" አማካኝት ይከፈላሉ፡፡

የጥርስ ህክምና እንዴት አገኛለሁ?

እርስዎ የጥርስ ህክምና የApple Health የአገልግሎት ክፍያ ከሚቀበል የጤና አገልግሎት ሰጪ ያገኛሉ፡፡ በአገልግሎት ክፍያ ዜዴ የሚሰራ አገልግሎት ሰጪ ለማፈላለግ ProviderOne Find a Provider search tool **https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider** ይመልከቱ፡፡

የትኞቹ የጥርስ አገልግሎቶችና ህክምናዎች ይሸፈናሉ?

የApple Health ሽፋን ያላቸው እድሜያቸው 21 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሁሉም አዋቂቆች የሚሰጡ የጥርስ አገልግሎቶች ዳሰሳ በ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-811.pdf** ይመልከቱ፡፡

እኔ የአይን ምርመራዎችን እና የአይን መነጸሮችን እንዴት አገኛለሁ?

የመንጸባረቅ እና እይታ ችግሮችን ጨምሮ የሚደረጉ የአይን ምርመራዎች በእርስዎ የጤና እቅድ ተቋም በኩል ይሰጣሉ፡፡

- እ ድሜያቸው እስከ 20 ዓመት ለሆኑ ልጆች - የመነጸር ፍሬሞች፣ የአይን መያዝ ሌንሶች እና የመግጠም አግልግሎቶች በApple Health የአገልግሎት ክፍያ ይሸፈናሉ፡፡
- ለአዋቂዎች— የመነጸር ፍሬሞች፣ የአይን መያዝ ሌንሶች እና የመግጠም አግልግሎቶች በApple Health የአገልግሎት ክፍያ አይሸፈኑም፤ ነገር ግን እርስዎ እነዚህን ዕቃዎች በቅናሽ ዋጋ ከሚያቀርቡ ተሳታፊ አገልግሎት ሰጪዎች ማዘዝ ይችላሉ፡፡. እርስዎ ተሳታፊ አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር በ **http://www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/Optical_Providers_Adult_Medicaid.pdf** ማፈላለግ ይችላሉ፡፡

በWashington Apple Healthና Medicaid መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

Washington Apple Health በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የMedicaid ስም ነው፡፡ የእርስዎ የጤና እርዳታ ሰጪ ወይም እግዳ ተቀባዩ Medicaid ብለው ሊጠሩት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው፡፡

ሌላ ምን ማወቅ ያስፈልገኛል?

ተጨማሪ መረጃዎች በ*Welcome to Washington Apple Health* የሚለው መጽሐፍ በ **www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf** እና እርስዎ ከጠና እቅድ ተቋም የሚቀበሉ ማቴሪያሎች ውስጥ ተካትተዋል፡፡

አስፈላጊ ድህረገጾች እና URLዎች

የድህረገፅ	URL
የመመዝገቢያ ቅጽ	www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/13-862.pdf
አገልግሎት ሰጪ (ክፍያ ዜዴ የሚሰራ ብቻ) ይፈልጉ	https://fortress.wa.gov/hca/p1findaprovider
ProviderOne Client Portal	https://www.waproviderone.org/client
Washington Healthplanfinder	www.wahealthplanfinder.org
ወደ Washington Apple Health እንኳን በደህና መጡ መጽሐፍ	www.hca.wa.gov/assets/free-or-low-cost/22-1298.pdf